# የጅማ ዩኒቨርሲቲና የጅማ ከተማ የግንኙነት ማስተባበርያ ፅ/ቤት

## የዕቅድ መነሻ ሐሳብ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

መጋቢት 2009 ዓ.ም

Contents

መግቢያ ..........0
የትብብራችን አቅጣጫ..........1
የትብብር አሰራር መልካም ተሞክሮዎች ..........2
የዕቅዱ መነሻ..........3
የዕቅዱ ዓላማ ..........4
ዋና ዋና ተግባራት ..........4
ለመነሻነት የቀረቡ የትብብር መስኮች ..........7

## መግቢያ

ተቋማችን ጅማ ዩኒቨርሲቲም ሆነ ዩኒቨርሲቲውን የመሠረቱት ሁለቱ ነባር ተቋማት ማለት የጅማ እርሻ ኮሌጅና  የጅማ ጤና ሣይንስ ከተመሰረቱበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ወቅቶች የአካባቢውን ማህበረሰብ ተሣታፊነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን ሲያከናውኑ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲም በ1992  ዓ.ም እንደ ዩኒቨርሲቲ በአዋጅ ከተቋቋመ በኃላ የስልጠናና የት/ት ሂደቱን በማህበረሰቡ ተኮር ትምህርትና ስልጠና ፍልስፍና በመቃኘት፤ የመማር ማስተማርና ከጥናትና ምርምር ስራዎች በተጨማሪ ለማህበረሰብ አገልግሎትን ተግባራት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፤ ብሎም ፍልስፍና የድህረ-ምርቃና የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች ስርዓተ-ትምህርት (curriculum) ውስጥ እንደ መደበኛ የት/ት ዓይነት እንዲካተት ተደርጓል፡፡በዚህም ተማሪዎቻችን በመማርያ ክፍሎች ውስጥ በንድፈሃሣብ የቀሰሙትን ዕውቀት በስራ ላይ እንዲያውሉት የሚያስችል የተግባር ስልጠና ዕድል ከመፍጠሩም በላይ የማህበረሰቡ ችግሮች የሚፈቱበት ሁኔታን አመቻችቷል፡፡

ከመደበኛው የማተትስ ባሻገር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና በመተግበር የማህበረሰቡን ችግሮች በመቅረፍ ብሎም የአካባቢውን ማህበረሰብ የልማት እንቅስቃሴ በመደገፍ ረገድም፤በግብርናና በእንስሣት ህክምና፣በጤና፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በትምህርት፤ በሕግ አገልግሎት መስኮች ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል ፡፡ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ለሚገኙ መንግስታዊ ተቋማትና ፤ የማህበረሰብ አባላት፤ የፋይናንስ ፤ የሙያና የማቴሪያል፣ ድጋፎችን በስፋት ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በጅማ ከተማና በጅማ ዞን ብሎም በሌሎች የሃገራችን ክፍሎች ላሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን የማህበረሰቡና ለማህበረሰቡ የተፈጠረ ተቋም መሆኑን ያስመሰከረ ተቋምነው።ላለፉት በተከታታይ አምስት ዓመታት በሃገራችን ከሚገኙ የት/ት ተቋማት መካከል በተከታታይነት አንደኛ የመውጣቱ አንዱ ሚስጥርም ይሄው በማህበረሰብ አገልግሎት መስክ ያስመዘገብናቸው አመርቂ ውጤቶች መሆኑ ግልፅ ነው።

እስካሁን በማህበረሰብ አገልግሎት መስክ ያስመዘገብናቸው ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው ባንድ በኩል ተቋማችን ካስቀመጠው ራዕይና ካለው ተቋማዊ ዓቅም ረገድ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰባችን ውስጥ ካለው የትብብር ፍላጐት ስፋትና ባህሪ አኳያ ሰፊ የትብብር መስኮችን መፍጠር፡ የፈጠርናቸውንም የትብብር መስኮችና ተግባራት ይበልጥ ማጠናከርና ማስፋፋት ይጠበቅብናል ። ይህንንም ስራችንን በደንብ በተደራጀና ራሱን በቻለ ዓብይ ዕቅድ በመመራት ማከናወን ይጠበቅብናል። ይሄም ዕቅድ ይሄንን ከላይ የተገለጠውን ሐሣብ ከግንዛቤ በማስገባት ፡ የማስተባበርያ ፅ/ቤቱ ሲቋቋም የተቀመጠውን የስራ ድረሻ መሰረት በማድረግ ለመነሻነት የተዘጋጀ ሲሆን፣በየደረጃው ከሚገኙ የሚመለከታቸው የአመራር አካላት ጋር በሚደረግ ውይይት እየዳበረ የሚሔድ ነው።

## የትብብራችን አቅጣጫ

ትብብራችን የሚመራበት ፍልስፍና በዋናነት የጋራ ጥቅምን ማዕከል በማድረግ ፤ የአከባቢው ማህበረሰብ የራሱ ልማት ባለቤትና አቃጅ ሆኖ ተቋማችን ደግሞ በአጋርነት የልማቱን እንቅስቃሴ የሚደግፍበት፤ ተቋማችንም የራሱን የእድገት አቅጣጫ በራሱ በመቀየስ የሚንቀሳቀስበት ይሆናል። በትብብር ሊሰሩ የታሰቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ተባባሪዎቹ አካላት በውይይት፤ በስምምነትና በእኩልነት በማቀድ፤ በትግበራውም ውስጥ

እንደ ትብብሩ መስክ ባህሪ የየራሳቸውን ኃላፊነትና ድርሻ የሚወጡበት እንጂ አንድ ሰጪ አንዱ ተቀባይ የሚሆንበት አይደለም፡፡

የማህበረሰቡን የልማት እንቅስቃሴ የመደገፍ አቅጣጫችን በተወሠኑ ጊዜያት የሚነሱ የቁሣቁስና የፋይናንስ ድጋፎችንና፣በተበጣጠሰ መልኩ ከምናካሂዳቸው ስልጠናዎችና እንቅስቃሴዎች ባሻገር ማህበረሰቡንና ተቋሙን በዕኩልነት ባሣተፈ መልኩ ለተወሠኑ ባለሙያዎች ከምንሰጣቸው የት/ት ዕድሎች ባለፈ በአከባቢው ያለውን የዓቅም ግንባታ ፍላጎትም ሌሎች የትብብር መስኮች ባገናዘበ መልኩ ራሱን የቻለ የጋራ ስትራቴጂ በማዘጋጀት የሚመራ ይሆናል፡፡ የጋራ በሆነ ገዢ ዕቅድ (strategic plan) የሚመራ ዘርፈ ብዙና ሁሉን አቀፍና ዘላቂ የትብብር መድረክ መፍጠር ማለታችን ነው፡፡ይሄ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ይሄንን ግንኙነት እንደ አንድ ቁልፍ ስራ በመውሰድ፣ መስራት ስንችል ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲያችን የመጀመሪያውን እርምጃ በመውሰድ የጅማ ዩኒቨርሲቲና የጅማ ከተማ ግንኙነት ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ራሱን ችሎ እንዲቋቋምና በዳይሬክተር እንዲመራ አድርጓል፡፡

ይህ እርምጃም ከዚህ ቀደም የምንሰራቸው የማህበረሰብ አገልግሎት ስራችንን በተደራጀና፣ ጉልህ በሆነ መንገድ መስራት እንድንችል ከማድረጉም በላይ ተቋማችን ከአካባቢው ጋር ያለውን ጠንካራ ትስስር ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በተቋማችን በኩል ያለውን ቁርጠኝነት በግልፅ የሚያመለክት ነው፡፡

## የትብብር አሰራር መልካም ተሞክሮዎች

ከከተማውም ሆነ ከዞኑ አመራር ብሎም ከአጠቃላይ ማህበረሰቡ ጋር በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በጋራ መንቀሣቀስ ለተቋማችን ዕድገትና ሠላም፣ብሎም ለአካባቢው ዕድገት

የማይተካ ሚና አለው። ከከተማውም ሆነ ከዞኑ የተለያዩ የመንግሰት አካላት ጋር በተለያዩ ወቅቶች በትብብር የመስራት ባህል አለን ። በቅርቡ እንኳን በስፖርት ዝግጅት ወቅት የፈጠርናቸውን የቅንጅት ስራዎችና በኮማንድፖስት ስራችን ያገኘናቸውን መልካም ልምዶች እንደ ምሣሌ መመልከት ይቻላል ።

በቅርቡ በዩኒቨርሲቲያችን አዘጋጅነት ሊካሄድ የነበረውን 9ኛው የስፖርት ፌስቲቫል ለማስተባበር የተቋቋሙትን የጋራ ኮሚቴዎችና የመማር ማስተማሩን ሂደት ሠላማዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን ተቋቁሞ በትጋት ሲንቀሣቀስ የነበረውን የኮማንድፖስት እንቅስቃሴዎችንና ውጤቶች በመመልከት መረዳት ይችላል።

በእነዚህ ኮሚቴዎች ውስጥ የከተማውና የዞኑ አመራሮች በባለቤትነት በመንቀሣቀሣቸው፤ በዚህ መስክ የዩኒቨርሲቲውን ዕቅድ የራሣቸው ዕቅድ ማድረግ በመቻላቸው፣ለብዙ ዓመታት ሲንከባለሉ የነበሩ ችግሮች እንዲፈቱ ከማስቻሉም በላይ ቀላል የማይባል ንቅናቄ መፍጠር እንደተቻለ የምናስታውሰው ነው ።በኮማንድፖስቱም ረገድ፣የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማደናቀፍ ይደረጉ የነበሩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ቀድሞ በመገንዘብና፣ በማክሸፍ የት/ት ሂደቱ የተቀመጠለት መርሃ ግብር ሣይዛነፍ እንዲጠናቀቅ ከማስቻሉም በላይ፣አንዳንድ ኮሌጆች (በተለይ እንደ ቴክኖሎጂ) ላይ የተስተዋሉ ትምህርት የማቋረጥ አዝማሚያዎች ስር ሣይሰድዱ በውይይት እንዲፈቱ ለማድረግ የዩኒቨርሲቲያችንና የከተማው እንድዉም  የዞኑ አመራሮች የተቀናጀ ርብርብ ዉጤት ነዉ ማለት ይቻላል።

## የዕቅዱ መነሻ

- በተቋማችን የሚከናወኑ የማህበረሰቡን የልማት እንቅስቃሴዎች የመደገፍ በተደራጀና በተቀናጀ መልክ በዘላቂነት ማከናወን።

- የአካባቢው ማህበረሰብና፣ አመራር ተቐማችንን በባለቤትነት መንፈስ እንዲመለከተው ማድረግና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማስራት
- የማህበረሰብ አገልግሎት ስራችንን ወደ ላቀ ደረጃ ማሣደግ

## የዕቅዱ ዓላማ

1. በዩኒቨርሲያያችንና በጅማ ከተማና ዞን አስተዳደሮች መካከል የሁለትዮሽ የሆኑ በጋራ መስራት የሚያስችሉ መደበኛ የሆኑ የጋራ አሰራሮችን ይዘረጋሉ
2. በዩኒቨርሲያያችንና በጅማ ከተማና ዞን አስተዳደሮች መካከል የሁለትዮሽ የሆኑ በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ የትብብር መስኮችን ይለያሉ
3. ዩኒቨርሲቲውና በሥሩ ያሉት የስራ ክፍሎች እንደ ተቋም ብሎም እያንዳንዱ በተቋሙ የሚገኝ ባለሙያ በአካባቢው ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ተሣትፎ ያደርጋሉ
4. ዩኒቨርሲቲያችን የሚያከናውናቸውን ዘርፈ ብዙ ስራዎችና በተመለከተ ያሉ ችግሮችን ከተማውና የዞኑ መስተዳድሮችና ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በጋራ መፍትሄ ያስቀምጣሉ
5. የከተማውና የዞኑ ማህበረሰብ ዩኒቨርሲቲያችንን የስራ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ በቂ ግንዛቤ ይጨብጣሉ

## ዋና ዋና ተግባራት

1. በከተማው በዞኑ ና በዩኒቨርሲቲያችን መካከል መደበኛ የሆነ የትብብር አሰራሮችን መዘርጋት

- ትብብሩን የሚያስተባብር፣ የሚመራ ዓብይ ግብረ-ሃይል ኮሚቴ (steering committee) ማቋቋም
- ሃላፊነቱን በዝርዝር ማስቀመጥ
- አባላቱን መለየት
- የአሰራር አግባቡን ማስቀመጥ
- የግንኙነት አግባብ ማስቀመጥ

2. በየስራ ዘርፉ የትብብር መድረኮችን ማዋቀር
    - በዋናነት የኮሌጆቻችንን አወቃቀር በተሣካ መልኩ ሆኖ ከዞኑና ከከተማው ፅ/ቤቶች ጋር በመሆን እንደ የስራ ባህሪ የሚቋቋም ይሆናል፡፡
    - የስራው ሁኔታ የአሰራር አግባቡ ከዓብይ ኮሚቴው አካሔድ ላይ የተመሠረት ሆኖ እንደ የስራ ባህሪው የተለዩ ሃላፊነቶችን ባካተተ መልኩ ይቋቋማል

3. የትብብር መስኮችን መለየት
    - ትብብር ሊደረግባቸው የሚችሉ መስኮችን ለመለየት

4. የፍላጐት ዳሠሣ ጥናት ማካሄድ
    - መጠይቆችን ማዘጋጀት ፡ በመጠይቅ
    - ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ
    - የትብብር መስኮችን ከጊዜ አኳያ /የአጭር፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ/ መለየት

- ❖ በትብብር መስኮቹ የሶስቱን አካላት ድርሻና ሃላፊነት መለየት
- ❖ የሶስትዮሽ ስምምነት መፈራረም
- ❖ የባለሙያዎች ቡድን በማዋቀር የፍላጎት ዳሰሳውን ጥናት ማከናወን

5. ዩኒቨርሲቲያችን የሚተገብራቸውን ፕሮጀክቶች በተመለከተ ከዞኑና ከከተማው መስተዳድሮች የተያያዙ ፍላጐቶችን መለየት
   - ✓ በተቋማችን የሚከናወኑና ለተፈፃሚነታቸው የዞኑንና የከተማው መስተዳድር ድርሻ ያለባቸውን ዘርፎች መለየት
   - ✓ ፕሮጀክቶቹን ለማከናወን ማነቆ የሆኑ ችግሮችን መለየትና ሰነዶችን ማዘጋጀት
   - ✓ ለትብብር ማስተባበሪያ ዓብይ ኮሚቴው እየቀረቡ የመፍትሔ አቅጣጫ እንዲቀመጥላቸው ማድረግ፣ተፈፃሚነታቸውን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሠሌዳና አቅጣጫ መሠረት መገምገም፡፡

6. የከተማውና የዞኑ ማህበረሰብ አካላት ስለዩኒቨርሲቲያችን የስራ እንቅስቃሴ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፡፡
   - ❖ እስካሁን የከናወናቸውን ተግባራትና በሂደት ላይ ያሉትን በመለየት /ፕሮጀክቶች፣የማህበረሰብ አገልግሎት የመሠረተ-ልማት እንቅስቃሴዎች በተመለከተ ፅሁፎችን፣ፎቶዎችንና ቪዶዎችን ማሣናይት
   - ❖ ከከተማውና ከዞኑ ከተውጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሣተፉባቸው ውይይቶች፣ሲምፖዚየም፣ ኢግዚቪሽን ማሣናይት

- ❖ በአካባቢያችን በሚገኙና የሚዲያ መንገዶች፣ ፕሮግራሞቻችን እንዲተላለፉ ማድረግ
- ❖ በኤፍ. ኤም ፕሮግራሞች መደበኛ የሆነ የተቋማችንን እንቅስቃሴ በተለያዩ መንገዶች ለህ/ሰቡ ማስተዋወቅ፡፡
- ❖ በከተማውና በዞኑ የሚገኙ የ1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች በተለያዩ ወቅቶች ተቋማችን የሚጐበኙበት ሁኔታ ማመቻቸት

## ለመነሻነት የቀረቡ የትብብር መስኮች

- ❖ አቅም ግንባታ የት/ትና ስልጠና ተቋም እንደመሆናችን መጠን ዋነኛው የትብብር መስካችን የአቅም ግንባታ መስክ ነው፡፡
  1. የአመራር አቅም ግንባታ
  2. የአስፈፃሚው አቅም ግንባታ
  3. የህብረተሰቡ አቅም ግንባታ
  4. የፈፃሚዎች አቅም ግንባታ

1. ከአጭር ጊዜ አኳያ
   - ❖ አጫጭር ስልጠናዎችን ማዘጋጀት

   (Toilor – made need – based) ከተወሰኑ ቀናት እስከ ሣምንታት የሚዘልቁ ስልጠናዎች

2. ከረጅም ጊዜ አኳያ

   ሀ. በተቋማችን ተከፍተው በመሰጠት ላይ ባሉ ፕሮግራሞች

   - ➢ በቀን፣ በማታ፣ በዊከንድ ፣በርቀት

   ለ. ራሱን የቻለ ፕሮግራም በማስናዳት በተለያዩ ዘርፎች፡፡ <u>ለምሣሌ</u>

   - ➢ በከተማ አመራር /urban planning and Management/

- Leadership and Governance / developmental leadership/
- ሴቶችንና ወጣቶችን ማብቃት (Women's and youths empowerment)
- ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የላቦራቶሪ ባለሙያዎችን በድፕሎማ ወይም ድግሪ ፕሮግራም ከፍቶ ማሰልጠን
- Consultancy and technical services
  - ✓ In various fields: legal services, Waste disposal, entrepreneurship, family planning and counseling, saving culture, land management, organizational development and etc.

3. የስልጠና መስኮች

- ❖ የግብርናና የእንስሳት ህክምና
  - ✓ የከተማ እርሻ (Urban Agriculture)
  - ✓ Afforestration እና ወ.ዘ.ተ
  - ✓ በእንሲሳት ልማት፤ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፤ በአግሮ ፕሮሴስንግ እና ወ.ዘ.ተ
- ❖ የጤናና፣ የከተማ ውበትና ፤ ፅዳት
  - ✓ በቤተሰብ ዕቅድ (Family planning)
  - ✓ በየግልና የአከባቢ ንፅዕና (Personal and environmental sanitation)
- ❖ በICT
  - ✓ በላይብራሪ
  - ✓ በዶክመንተሽን
- ❖ ነፃ የህግ አገላግሎት (free legal services)
- ❖ Free business advisory

- ❖ በመልካም አስተዳደር ዙሪያ
- ❖ በቴክኖሎጂ ሽግግር (technology transfer)
- ❖ በGeography and Enviromental Studies (GIS)
- ❖ በት/ት በተፈጥሮ ሣይንስ፣ በማህበራዊ ሣይንስ፣ በት/ት አመራር፣ በጐልማሶች ት/ት መስክ
- ❖ ከከተማዉ አስተዳደርና ከዞን አስተዳደር ሞዴል ት/ቤት መኖር
- ❖ የተማሪዎች የቋቋን ክህሎት (English language proficiency) መሻሻልና ዉጤታቸዉን ለማሳደግ መስራት
- ❖ ባህልን ማስተዋወቅ በተለይ ከጅማ አባ ጅፋር ቤተ-መንግስት ጋር ተያይዞ አስፈላጊዉን ሥራ መስራት
- ❖ Tourism ላይ መስራት
- ❖ የዉጭ እና የ ህዝብ ግኑኝነት ሥራዎችን መስራት / መጠናከር
- ❖ በምህንድስና ዘርፍ (የከተማ፤ ኮንስትራክሽን)
- ❖ Building digital library and library automation for Jimma town public library (by ICT and library)
- ❖ Capacity building training for Jimma town and Jimma zone librarian
- ❖ Capacity building training for Jimma town and Jimma zone record keepers (by library)
- ❖ Capacity building training for Jimma town and Jimma zone ICT technician
- ❖ Office machine maintenance and trouble shooting for Jimma town and Jimma zone (by ICT)
- ❖ Developing standardized websites for Jimma town and Jimma zone (if not yet)

- ❖ Soft ware development (E.g., roster development for grade 8 students of Jimma town and Jimma zone)
- ❖ Consulting and designing library platform for Jimma town and Jimma zone
- ❖ Wired and wireless network installation for Jimma town and Jimma zone
- ❖ Designing and building data center for Jimma town and Jimma zone (by ICT)
- ❖ የዩኒቨርሲቲዉን ድንበር ወሰን ማስከበር ( for all campuses of JU)
- ❖ ለከተማዉ የቆሻሻ ማስወገጃ መብለያ ገንዳ (Oxidation Pond) አስፈላጊዉን ድጋፍን ክትትል ማድረግ
- ❖ ለዩኒቨርሲቲዉ የዉስጥ ገቢ ማመንጫ ለይ ከሚመለከተዉ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊዉን ሥራ ማስራት
- ❖ በጅማ ከተማ ዉስጥ በሀገር ደረጃ ልሰራ የታቀደዉን ኢንዳስትሪ ፓርክ ዩኒቨርሲቲያችን የበኩሉን ድርሽ እንድወጣ ማድረግ
- ❖ ፎረሞችን ማዘጋጀት፡፡ ለምሣሌ **Clean and Green Jimma Town Forum**
- ❖ የአከባቢዉ ጸጥታ ጉዳይ (JU Campuses and Jimma Town's security issues)
- ❖ ዘርፈ ብዙ ችግር ፈቺ ምርመሮችን መስራት (Joint multi disciplinary research endeavors)
- ❖ በፋይናንስና ቢዝነስ አስተዳደር እና ወ.ዘ.ተ. ናቸዉ

# የድርጊት መረሀ ግብር

| ተ.ቁ | ክንዉን | ጊዜ | ሃላፊነት | ተሣታፊዎች |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ግብረ ሀይል ኮሚቴ መቋቋም (Steering Committee)<br>A. የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝዳንት<br>B. የከተማዉ ከንቲባ<br>C. የከተማዉ ሥራ አስኪያጅ<br>D. የዞን አስተዳዳሪ<br>E. የድርጅት ቢሮ ኃላፊዎች<br>(የከተማዉና የዞን) | መጋቢት 2009 | የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝዳንት፣ የከተማዉ እንዲዉም የዞን አስተዳደር | የግብረ ሀይል ኮሚቴ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | የፍላጎት ዳሠሣ ጥናት ማካሄድ | ሚያዝያ 2009 | የፓርትነርሽፕ ቢሮ | የግብረ ሀይል ኮሚቴ |
| 3 | የትብብር መስኮችን መለየት | ግንቦት 2009 | የፓርትነርሽፕ ቢሮ | የግብረ ሀይል ኮሚቴ |
| 4 | ከምመለከታቸዉ ባለድሻ አካላት ጋር ግንዛቤ መፍጠር | ሰኔ 2009 | የፓርትነርሽፕ ቢሮ | የግብረ ሀይል ኮሚቴ |
| 5 | የትብብር ሥራዎችን የትግበራ ዕቅድ ማዘጋጀት | ሐምሌ 2009 | የፓርትነርሽፕ ቢሮ | የግብረ ሀይል ኮሚቴ |